በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
የኮሙኒኬሽንና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምሪያ
በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ ዜና-መጽሔት ቁ.54
Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations
Communication and International Relations Department
Bi-monthly News Letter No.54

## የምክር ቤቱ ዋና ፀሐፊና ምክትላቸው በዓለም አቀፉ የምክር ቤቶች ኮንግረስ ላይ ተሳተፉ

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ፀሐፊ አቶ ጋሻው ደበበ እና ምክትላቸው አቶ እንዳልካቸው ስሜ በካታር ዶሀ በተካሔደው 8ኛው የዓለም ምክር ቤቶች ኮንግረስ የኢትዮጵያን የግል ዘርፍ በመወከል ተካፈሉ፡፡

አቶ እንዳልካቸው ስሜ ለኢትዮ-ቻምበር እንደገለፁት ከሚያዚያ 13-16 ቀን 2005ዓ.ም. **'መልካም ዕድሎች ለሁሉም'** በሚል መሪ ቃል በዓለም አቀፉ የንግድ ምክር ቤት፣የአለም አቀፍ ንግድ ምክር ቤቶች ፌዴሬሽን እና በአለም አቀፍ የምክር ቤቶች ኮንግረስ ጥምር አዘጋጅነት የተካሄደው ኮንግረስ በዓለም እጅግ የታወቁ ፓነሊስቶች እንዲሁም ከፍተኛ ልምድና ዝና ያላቸው ሰዎች ነበር ብለዋል፡፡

በዓመት ሁለት ጊዜ የሚደረገው ይህ ታላቅ ኮንግረስ በመላው ዓለም የሚገኙ የንግድ ምክር ቤቶች አመራር አካላት እውቀትና ልምድ የሚለዋወጡበት፣ በጋራ ለመስራት የውይይት መድረክ የሚፈጥሩበት እንዲሁም ዓለም አቀፍ ልምድን በመቅሰም ወደ ሀገራቸው ሲመጡ ያገኙትን ልምድ ተጠቅመው የተሻለ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ የሚያግዝ መልካም አጋጣሚን የፈጠረ ነው ሲሉ ምክትል ዋና ፀሐፊው ተናግረዋል፡፡

ከመቶ ሀገሮች የተወጣጡ ከ12,000 በላይ ተሳታፊዎችን ያካተተው ይህ ታላቅ ኮንግረስ የትልልቅ ኩባንያዎች ዋና ሥራ አስፈፃሚዎችን ጨምሮ ታላላቅ የዓለም መሪዎች የተካፈሉበት

## 4ኛው የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ስብሰባ ሊካሄድ ነው

4ኛው የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ስብሰባ ግንቦት 27 ቀን 2005ዓ.ም. ቀን በሂልተን ሆቴል ይካሄዳል፡፡

በተያዘው መርሀ ግብር መሰረት ከጠዋቱ 3 ሰዓት ጀምሮ የሚካሄደው ስብሰባ በርካታ የውይይት አጀንዳዎችን ያካተተ ሲሆን ከአባል ምክር ቤቶች ጋር ስለተደረጉ ትብብሮች የተዘጋጀ ሪፖርት የሞደመጥበት፣ በአባል ምክር ቤቶች መካከል ያሉ በጎ ተሞክሮዎች ቀርበው የሚፀድቁበት እንዲሁም ኢትዮጵያ የጀመረችውን የዓለም የንግድ ድርጅት አባልነት ድርድር ሂደትና የተደረሰበትን ደረጃ ለምክር ቤቱ ሰራተኞችና አባል ምክር ቤቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ገለፃ የሚደረግበት እንደሚሆን ለመረዳት ተችሏል፡፡

## በደቡብ ኮርያ ለሚካሄደው የኢትዮ-ኮርያ ቢዝነስ ፎረም ምዝገባ ተጀምረ

በደቡብ ኮርያ ሲኡል ከተማ ከሰኔ 26-30 ቀን 2005ዓ.ም. በሚካሄደው የኢትዮ-ኮርያ ቢዝነስ ፎረም እና ከ50 ዓመታት በፊት የተጀመረውን የሁለቱ ሀገሮች ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ለማስታወስ በተዘጋጀው ፕሮግራም ላይ ለመሳተፍ የሚፈልጉ የንግዱ ማኅበረሰብ አባላትን የመመዝገብ ሥራ ተጀመረ፡፡

ምዝገባውን የሚያከናውነው የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ሲሆን አስፈላጊውን ፎርማሊቲ .....

አድራሻ፣ፋክስ፡ - +251-011-5517699
ኢ-ሜይል: ethchamb@ethionet.et
ደረ-ገጽ፡- www.ethiopianchamber.com

በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
የኮሙኒኬሽንና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምሪያ
በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ ዜና-መጽሔት ቁ.54
Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations
Communication and International Relations Department
Bi-monthly News Letter No.54

የሚያሟሉ በማንኛውም የንግድ ዘርፍ የተሰማሩ የምክር ቤቱ አባላት ሁሉ መካፈል እንደሚችሉ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ፎረሙ በተጨማሪም ከኮርያ የንግዱ ማኅበረሰብ አባላት ጋር በእሽሙር ለመስራት መልካም አጋጣሚ የሚፈጥር እንደሆነ ከወዲሁ ለመረዳት ተችሏል፡፡

## በምክትል የንግድ ሚንስትሩ የሚመራ የስዊድን የንግድ ልዑካን ይመጣሉ

በምክትል የንግድ ሚነስትሩ የሚመራ ከፍተኛ የስዊድን የንግድ ልዑካን በኢትዮጵያ ያለውን የኢንቨስትመንት ሁኔታ ለማጤን ግንቦት 8 ቀን 2005ዓ.ም. በምክር ቤቱ ተገኝተው ከምክር ቤቱ አመራር ጋር እንደሚወያዩ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ስዊድን በኢትዮጵያ በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች ለመሰማራት ከፍተኛ ፍላጎት እያሳዩ ከመጡ የአውሮፓ ሀገራት መሀከል አንዷ ስትሆን በቅርቡ በኢትዮጵያ የስዊድን አምባሳደር ከምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት ወ.ሮ ሙሉ ሰለሞን ጋር ባደረጉት ውይይት በርካታ የስዊድን የንግዱ ማኅበረሰብ አባላት በቅርቡ የሀገሪቱን ኢንቨስትመንት ሁኔታ ለማጤን እንደሚመጡ መግለፃቸው ይታወሳል፡፡

## ሀያ አራት ቡድን የያዘ የንግዱ ማኅበረሰብ አባላት ወደ ጣሊያን ሊሄድ ነው

ሀያ አራት አባላትን ያካተተ የኢትዮጵያ የንግድ ልዑካን ቡድን በጣሊያን ከግንቦት 15-18 ቀን 2005ዓ.ም. በሚካሄደው የኢትዮ-ኢታሊ የቢዝነስ ፎረም ላይ ለመካፈል እንደሚሄዱ ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይገልፃል፡፡

ከሁሉም የንግድና ኢንቨስትመንት መስክ የተወጣጡ አባላትን ያካተተው የልዑካን ቡድን በጣሊያን ቆይታቸው የልምድ ልውውጥ እንደሚያደርጉና ከጣሊያን አቻዎቻቸው ጋር በእሽሙር የሚሰሩበትን መልካም አጋጣሚ ሊገጥማቸው እንደሚችል ይጠበቃል፡፡

## የቱርክ የንግድ አታሼ በምክር ቤቱ ጉብኝት ሊያደርጉ ነው

የቱርክ የንግድ አታሼ ሚስተር ኪሊሽ ግንቦት 8 ቀን 2005ዓ.ም. በምክር ቤቱ ተገኝተው ከምክር ቤቱ አመራር አካላት ጋር በሁለቱ ሀገራት መሀከል ስላለው የንግድ ለንግድ ግንኙነት ለማጠናከር በሚቻልባቸው መንገዶች ዙሪያ እንደሚመክሩ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ቱርካዊያን ባለሀብቶች በኢትዮጵያ በርካታ ሚሊዮን ዶላሮችን በማፍሰስ በጨርቃ ጨርቅ እና በግብርና ማቀነባበሪያ የኢንዱስትሪ መስኮች ተሰማርተው የሚገኙ ሲሆን ከቻይናና ከህንድ ቀጥሎ በሀገራችን የኢኮኖሚ እድገት እንቅስቃሴ ከፍተኛ ሚና ያላቸው ናቸው፡፡

## የዓለም አቀፉ የወሊድ ማዕከል በኢትዮጵያ ያለውን የኢንቨስትመንት ሁኔታ ለማጤን ሊመጡ ነው

ተቀማጭነቱ በህንድ የሆነው የዓለም አቀፉ የወሊድ ማዕከል (International Fertility Center) ኃላፊዎች በኢትዮጵያ ያለውን የኢንቨስትመንት ሁኔታ ለማጤን በያዝነው በግንቦት ወር 2005 ዓ.ም. ሊመጡ ነው፡፡ .....



አድራሻችን: - +251-011-5517699
ኢ-ሜይል: ethchamb@ethionet.et
ደረ-ገጽ:- www.ethiopianchamber.com

በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
የኮሙኒኬሽንና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምሪያ
በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ ዜና-መጽሔት ቁ.54
Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations
Communication and International Relations Department
Bi-monthly News Letter No.54

ከህንድ አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ዝና ያተረፈው ማዕከሉ በኢትዮጵያ በሚኖረው ቆይታ በሀገሪቱ ያለውን የኢንቨስመንት ሁኔታ በዋናነት ለማጤን የሚመጡ ሲሆን የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከቅዱስ ገብርኤል እና ከቅዱስ ያሬድ ሆስፒታሎች ጋር ልዑካኑን ለማገናኘት ፕሮግራም መያዙን ታውቋል:: ከሆስፒታሎቹ ጋር የሚያደርጉት ውይይት በሀገራችን ስላለው የጤና ዘርፍ ኢንቨስትመንት በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያግዝ ከመሆኑም በላይ ምናልባትም በእሽሙር ለመስራት መግባባት ላይ ሊደርሱ እንደሚችል ከወዲሁ ይጠበቃል::

ከዚህ በተጨማሪም ማዕከሉ ሌሎች የኢንቨስትመንት አማራጮችን እንደመሚመለከቱ ለመረዳት ተችሏል::

ማዕከሉ በህንድ የላቦራቶሪ ዕቃዎችን የሚያመርትና ለገበያ የሚያቀርብ እንደሆነም መረጃዎች ያሳያሉ::

## የሀገር አቀፉ ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ስልጠና አዘጋጀ

የኢትዮጵያ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከተለያዩ የኢንዱስትሪ ዘርፎች ለተወጣጡ የሥራ ሀላፊዎችና የድርጅት ባለቤቶች ከግንቦት 8 ቀን 2005ዓ.ም. ጀምሮ ለአራት ተከታታይ ቀናት የሚቆይ ስልጠና በአዳማ ከተማ አዘጋጀ::

በግሉ ዘርፍ ማበልፀጊያ ማዕከል (PSD hub) የፋይናንስ ድጋፍ የተዘጋጀው ስልጠና የአመራር ብቃትን ለማሳደግ የሚረዳ Transformational leadership)ላይ ያተኮረ ሲሆን ተሳታፊዎች ከተለመደው የማኔጅመንት ሙያ በተጨማሪ እጅግ ተመራጭ ወደሆነውና

በአደጉት ሀገራት በተጨባጭ ለውጥ በማምጣቱ የሚታወቅ አስተዳደራዊ ዘዴ የተሻለ ግንዛቤ የሚያገኙበት ነው::

ስልጠናውን የሚሰጡት በኢትዮጵያ አየር መንገድ በዋና ስራ አስፈጻሚነትና በተለያዩ የአመራር ደረጃዎች ከፍተኛ ልምድ ያዳበሩት አቶ ብስራት ንጋቱ እንደሆነ ከሀገር አቀፉ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የተገኘው መረጃ ይጠቁማል::

## የቡራዩ ከተማ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የንግድ ትርዒትና ባዛር ሊያዘጋጅ ነው

የቡራዩ ከተማ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከግንቦት የሚቆይ የኦሮሚያ ኢንዱስትሪ ሳምንት በሚል መርህ ቃል ግንቦት 17-25 ቀን 2005 ዓ.ም. የሚቆይ የንግድ ትርዒትና ባዛር ሊያዘጋጅ ነው፡

የቡራዩ ከተማ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳን ና የሀገር አቀፉ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ወ.ሮ አልማዝ ዘርጋው በተለይ ለኢትዮ-ቻምበር እንደገለፁት የኦሮሚያ የኢንዱስትሪ ሳምንት ሲከበር ለመጀመሪያ ጊዜ እንደሆነ በመግለፅ ለዝግጅቱ የከተማው መስተዳድር፣ የኦሮሚያ ከተማ ልማት ቢሮ እና የኦሮሚያ ክልል የኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ድጋፍ እንደሚያደርግላቸው ገልፀዋል::

አድራሻ፡ፋክስ: - +251-011-5517699
ኢ.ሜይል: ethchamb@ethionet.et
ድረ-ገጽ:- www.ethiopianchamber.com